## አዎንታዊ እምነት፣ አዎንታዊ ዝምድና፣ አዎንታዊ የትምህርት ሂደት እና አዎንታዊ ሽርክና በሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች

ውጤታማ የሆነ ትምህርት የሚፈጠረው ደህንነቱ በተጠበቀ አዎንታዊ፣ ቀጣይነት ያለው እና ውጤቱ የሚታወቅ ኣከባቢ ሲፈጠር ብቻ ነው። የባህላዊ ብስለት፣ ደህንነት፣ መከባበር፣ ቅንነት፣ ተጠያቂነት እና ርትዓዊ መሰረት ሓሳቦች መላው ስርዓት ውስጥ ሲገነቡ፤ መተማመን የሞላበት ግኑኝነት ይፈጠራል። ይህ ደግሞ ለያንዳንዱ ተማሪ ምርጥ የሆነ ትምህርት ለማደረስ ያስችላል።

የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች በወረዳው ውስጥ በት/ቤቶችና በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ብዙህነትን የሚያከብር እና ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጥ ባህላዊ ብስለትን (ካልቸራል ኢንተለጀንስ) ለማስፋፋት ቃል ገብቷል። ይህ ደግሞ ርትዓዊ እና መልካም ኣያያዝ ለሁሉም እንዲኖር ወሳኝ መመሪያ ሆኖ ያገልግላል።

የተጠበቀ እና ጤነኛ የትምህርት ቤት ኣከባቢ መኖር እያንዳንዱ ተማሪ የባለቤትነት ስሜት እንዲኖረው እና ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም ለማዳረስ ያስችላል። መልካም የትምህርት ቤት ኣከባቢ የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

- ራዕይ ላይ የተመረኮዘ የጋራ እምነት፣ ዋጋ የምንሰጠው ነገር፣ ኣምልኮ እና የባህሉ ኣካል ሆኖ ኣብሮ የሚያድገው ታሪክ።
- በጋራ ትብብርና መከባበር ላይ የተመሰረተ በተማሪዎች: በወላጆችና በሰራተኞች መካከል ያለ ግንኙነት።
- ሁሉንም ባህሎች የሚያከብር እና ዋጋ የሚሰጥ ኣግባብ ያለው እና ሁሉንም በኣንድ ዓይን የሚያይ ኣያያዝ።
- ሁሉንም በመልካም ሁኔታ የሚቀበል፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ለሁሉም ክፍት የሆነ የስራ ኣከባቢ።
- መደበኛ የሆነ በተማሪዎች፣ በቤተሰቦች፣ የትምህርት ቤት ባልደረቦች እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኣካላት የሚካሄድ የትምህርት ቤት ሁኔታን የሚያጠና ግምገማ እና ዳግም ጥናት።

መልካም (አዎንታዊ) የትምህርት ቤት ኣካባቢን ከመፍጠር በተጨማሪ ኣንዳንድ ጊዜ ተማሪዎች በስሜትና በአካላዊ ውጥረት ሊሰቃዩ እንደሚችሉ እንረዳለን። እንደዚህ ባሉ ጊዜያት ተማሪዎች የሚያስጨንቃቸውን ነገር ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚያምኑት ኣዋቂ ማካፈል በተጨማሪም ለሌሎች የትምህርት ቤት ባልደረቦች ማካፈል ይችላሉ። የትምህርት ቤት ባልደረቦችም ሁሉም ተማሪዎች ጥሩ ተሰምቷቸው ትምህርትታቸውን እንዲከታተሉ ከማገዝ አኳያ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋሉ::

ኣንዳንድ ጊዜ ተጨማሪ የምክር ኣገልግሎት፣ ድጋፍ እና ግብዓቶች ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ። ጤና እና ሰብኣዊ ኣገልግሎት በተመለከተ በጣም ብዙ ኤጀንሲዎች የተለያየ እገዛ እና የምክር ኣገልግሎት ለኪንግ ካውንቲ ነዋሪዎች የሚሰጡ ኣሉ። ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 800-621-4636, 206-461-3610 ወይም 211 ይደውሉ።

ይህ የተማሪዎች ሓላፊነት እና መብቶች ዶክመንት የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች የተማሪዎች ስነ-ስርዓትን ኣስመልክቶ ያስቀመጣቸውን ሕጎች እና መመሪያዎች ያዘለ ነው። ይህ ዶክመንት ከዋሽንግተን ስቴት መመሪያዎች እና የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች ስትራቴጅያዊ ውጥን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው። የዋሽንግተን ስቴት የመስተዳድር ሕግ (ዋሽንግተን ስቴት ኣድሚኒስትሬቲቭ ኮድ (WAC)) የእርምት ምላሹን አጠቃቀም የሚመራ ላይ የሰፈሩትን ለምሳሌ ስነስርዓት፣ መታገድ እና መባረር ኣስመልክተው የሰፈሩትን የማረሚያ እርምጃዎች መሰረት ያደረገ ነው።

የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች የስነስርዓት እርምጃ ፖሊሲ መሰረቱ ሁሉንም ትምህርት ቤቶች ያካተተ መልካም የትምህርት ቤት ኣከባቢ መፈጠር ነው። የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች የዲስፕሊን ፖሊሲ ከመከላከያዎች አንዱ ሲሆን አዎንታዊ የት/ቤት አካባቢን አካቶ በሚጠበቁ የጋራ ባህሪ እና ቋንቋ ላይ ከተማሪዎች: ወላጆች: አስተማሪዎች : አስተዳዳሪዎች: በጎ ፈቃደኞችና ሌሎች ሰራተኞች ጋር በተለየ መልኩ ንግግር ያደርጋል:: የስነስርአት እርምጃዎች እና ጣልቃ ገብ ስልቶች ዓላማው የትምህርት ሰአትን በኣግባቡ ለመጠቀም እና በስነምግባር እርምጃ ምክንያት የሚባክነው የትምህርት ግዜ ለመቀነስ ነው:: ይህ ደኩሜት ሁሉም ተማሪዎች ላይ እኩል ይተገበራል። በተጨማሪ ይህ ደኩሜንት ሁሉንም የትምህርት ማህበረሰብ ኣባላት ከትምህርት ጋር የተሳሰሩ ሕጎች፣ መመሪያዎች እና የሕግ ኣፈጻጸም ደንቦችን ለማስተማር ዓልሞ የተዘጋጀ ነው። ቤተሰቦች ይህን የተማሪዎች መብት እና ሓላፊነቶች የሚለውን ዶኩሜንት ከልጆቻቸው ጋር ሆነው እንዲያነቡት እንጠይቃለን። ዶክሜንቱ በት/ ቤት ውስጥ የሚጠበቀው እና ተማሪዎች በት /ቤት ውስጥ ከኣዋቂ ሰዎች የሚጠብቁት ይገልጻል::

### *የሲያትል የህዝብ ት/ ቤቶች ለማድረግ ቃል የሚገባቸው:*

*የ እድል ልዩነቶችን ማጥበብና ለሁሉም ተማሪዎች የትምህርት ልቀትን ማረጋገጥ የወቅታችን ጉዳይ ነው::*

*የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች የሚከተሉትን ይገነዘባል:*

- *በወረዳው የዲስፕሊን ግብረመልሶች ውስጥ የዘር ልዩነት እንዳለ::*
- *እያንዳንዱ ዲስፕሊንን የሚመለከት ጉዳይ በጣም የተወሳሰበና ሊሆን ስለሚችል ሰራተኞች የተማሪዎችን ባህሪ መረዳት እንዳለባቸው;*
- *ድብደባና የሚያባብሱ ነገሮች በዲስፕሊን የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር:: እና*
- *የማጭበርበር ድርጊቶች ተጽዕኖ እንደሚያመጡ:*

### *የሲያትል የህዝብ ት/ ቤቶች ሰራተኞች የሚከተሉትን ለማድረግ ይጥራሉ:*

- *ተማሪዎችን ማወቅ : አዎንታዊ ግኑኝነት መፍጠርና መንከባከብ*
- *ለልጁ ሁለንተናዊ ድጋፍ መስጠት*
- ***ሁሉንም ተማሪዎች ከፍተኛ ተስፋ ውስጥ በማስገባት፣ ጥራት ያለውና ውጤታማ የሆነ ትምህርት ማቅረብ***
- *የተማሪዎች አዎንታዊ የማህበራዊ, ስሜታዊ, እና ባህሪ ክህሎቶችን ማሳደግ*
- *ጉዳት ከተከሰተ በኋላ በማግለል ተግባራት ላይ ከመደገፍ ይልቅ ባህሪውን ለማስተካከል የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ::*
- *የተማሪና የት/ ቤት ግኑኝነትን በጥቂቱ ብቻ ሊጎዳ የሚችልን የዲስፕሊን እርምጃን ተግባራዊ ማድረግ የትምህርት ሰዓት ብክነትን ይቀንሳል::*
- *የቅጣት እርምጃ በተወሰደ ጊዜ ከቤተሰቦች: ከሌሎች ሰራተኞች እና ከማኅበረሰብ ተቋማት ጋር መተባበር: እና*
- *ከባህላዊ ምላሽ አኳያ ስሜታዊ የንግግር ክህሎቶችን በመጠቀም የራሳቸውን ውጫዊ መሰረት በመመርመርና የድንገተኛ ስነምግባር ክህሎቶችን በመፍጠር ተማሪዎችን ዉጤታማ ማድረግ ነው::*

## ተልዕኮ

የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች ፍትሃዊነት ያለው አቅርቦት መኖሩን በማረጋገጥ:
የአማራጭ ክፍተቶችን በመዝጋት እና ጥራት ያለውን ትምህርት ለእያንዳንዱ ተማሪ ለማዳረስ በትጋት ይሰራል::

## ራዕይ

እያንዳንዱ የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች ተማሪ ከፍተኛ ጥራት ያለውን የ 21ኛውን ክፍለ ዘመን ትምህርት እንዲያገኝ እና ተመራቂዎች ለኮሌጅ: ለስራ እና ለህይወት ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ ነው::

### የፍትሓዊነት እና የታዛዥነት/ Compliance/ ፖሊሲ

የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች (SPS) ለሁሉም እኩል እና ርትዓዊ የትምህርት እና የስራ ዕድል ይሰጣል። እንዲሁም በሁሉም ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ላይ ያለምንም የዘር፣ የቀለም፣ የብሔር፣ ጾታ፣ ሃይማኖት፣ ዕድሜ፣ የትውልድ ኣገር፣ ሃብት እና ገንዘብ፣ የአካል ጉዳተኝነት፣ ጾታዊ ዝንባሌ ማለትም የሆነ ሰው የሚጠራበት ጾታ ወይም መለያ፣ እርግዝና፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ኣካላዊ ቅርጽ፣ የሆነ የኣእምሮ ወይም የኣካል ጉዳተኛነት ወይም በክብር የተሸኙ ወታደሮች እና ኣርበኝነት፣ ወታደር መሆን ወይም የሰለጠነ መሪ ውሻ ወይም ሌላ እንስሳ በመጠቀም ልዩነት ሳያደርግ ለሁሉም ሰው እኩል ዕድል ይሰጣል። SPS ለሁሉም የተመደቡለት ወይም ተወክለው የመጡ እንደ ቦይ ስካውት እና ሌሎች የወጣቶች ማህበራት እኩል ዕድል ይሰጣል። ለተማሪዎች እና ለሁሉም የማህበረሰብ ኣባላት የሚከተሉት የመ/ቤቱ ሰራተኞች ጥያቄዎችን ሊመልሱና እና የተፈጸመ መድልዎ አቤቱታዎችን ሊቀበሉ የተመደቡ ስለሆነ ከታች ከተገለፁት በደብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜይል ልታገኙዋቸው ትችላላችሁ።

Seattle Public Schools
MS 32-149, PO Box 34165,
Seattle, WA 98124-1166

ወይም በስልክ ቁጥር ወይም ኢሜል ቀጥሎ ለየጉዳዩ በተዘረዘረው መሰረት ልታገኙዋቸው ትችላላችሁ።

ለጾታዊ ልዩነት ጉዳዮች ጾታዊ ጥቃትን ጨምሮ (ሴክሽዋል ሃራስመንት) የታይትል *IX ቅሬታ አስተባባሪ:* *Title.IX@seattleschools.org*

ለአካል ጉዳተኝነት አድልዎ ጉዳዮች : የADA/ ክፍል *504 ቅሬታ አስተባባሪ:* accessibility@seattleschools.org

ለሌሎች የአድልዎ ጉዳዮች በሙሉ ቀጥሎ ያለውን ክፍል ያግኙ:

የተማሪዎች ሰብአዊ መብቶች አስተባባሪ: oscr@seattleschools.org

አካል ጉዳተኝነት የተያያዘ ስለሚሰጥ ኣገልግሎት ወይም ስለሚደረግ አድልዎ: ጾታዊ በደልን ጨምሮ በሰራተኞች በኩል የሚነሳ ቅሬታ፡ ለመሳሰሉት:

የሰው ሃይል ልማት ምክትል ዋና አስተዳዳሪ
*Seattle Public Schools Mailstop 33-157, PO Box 34165*
*Seattle WA, 98124-1166* ወይም ስልክ ቁጥር (206) 252-0024 ወይም
hreeoc@seattleschools.org ያግኙ:


የሲያትል ት/ቤቶች የቦርድ አባላት:

Rick Burke — Eden Mack
Zachary DeWolf — Betty Patu
Leslie Harris — Scott Pinkham
Jill Geary

የበላይ አለቃ
Denise Juneau


Amharic

# የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች

## የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች መሰረታዊ ደንቦች

2018 - 2019



SEATTLE PUBLIC SCHOOLS

## የተማሪዎች መብቶች

የትምህርት ማህበረሰቡ ኣባላት እንደመሆናቸው መጠን ተማሪዎች የሚከተሉት መብቶች ኣሏቸው፤

- ስርዓትን የጠበቀ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ክፍል እና ትምህርት ቤት፤
- ተገቢ እገዛ ያለው እና እያንዳንዱ ተማሪ ላይ ከፍተኛ ተስፋ የሚጥል ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት፤
- ኣክብሮ ያለው እና ትህትና የሞላው ኣያያዝ፤
- እንዲደመጡ እና ሓሳባቸው እንዲሰማ፤
- ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት፣ አገልግሎቶች፣ግብኣቶች፣ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች በእኩልነት ማግኘት
- ትምህርት ቤት መኖራቸው መታወቅ እና በእንክብካቤ መያዝ፤ እና
- በደላቸውን የሚመጥን መቀጮ ማግኘት እና ከበደላቸው እንዲማሩ እድል ማግኘት።

በተጨማሪ ተማሪዎች ዜጎች እንደመሆናቸው መጠን ህገ መንግስታዊ መብት ኣላቸው ስለዚህ ትምህርት ቤት ያለምክንያት መብታቸውን መጋፋት ኣይችልም። ሆኖም ግን ትምህርት ቤት ተማሪዎች የመማር ሓላፊነታቸው እንዲወጡ እነዚህን መብቶች ገደብ ሊያደርግባቸው ይችላል።

- የመናገር ነጻነት
- የመሰብሰብ
- የድጋፍ ፊርማ ማሰባሰብ
- የመገናኛ ብዙሃን
- ምክንያት የሌለው ፍተሻ እና መታሰር የሌለበት
- እኩል የትምህርት እድል
- የእምነት

## የተማሪዎች ሓላፊነቶች

የትምህርት ማህበረሰቡ ኣባላት እንደመሆናቸው መጠን ተማሪዎች የሚከተሉት ጉዳዮች ላይ በግል ሓፊነት መውሰድ ኣለባቸው፤

- ትምህርት ቤት ውስጥ የሚያምኑት ኣዋቂ ሰው ጋር ኣእምሮኣቸውን፡ ስሜታቸውን እና ኣካላቸውን የሚጎዳና የሚያስጨንቃቸው ነገር ካለ ስለዚህ ጉዳይ መረጃ እና ድጋፍ ለማግኘት ማማከር ይችላሉ።
- ትምህርታቸውን፣ የባህላቸውን፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ ሁኔታቸውን የሚመለከቱ ነገሮች ለማስከበር መጣበቅ።
- ከሌሎች ተማሪዎች እና የትምህርት ማህበረሰቡ ኣባላት ጋር እርስ በርስ መከባበር ላይ የተመሰረት ግንኙነት መፍጠር።
- ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን ስነስርዓት ሳያሟሉ ሲቀሩ እና ከስተታቸው እንዲማሩ የተሰጣቸውን እድል ባግባብ ሳይጠቀሙበት ሲቀሩ ተመጣጣኝ የሆነ መቀጮ እንደሚወሰንባቸው ማወቅ።
- ትምህርት ቤት በመደበኛ ሁኔታ መከታተል እና ወደ ሁሉም ክፍል እኩል መዘጋጀት።
- ደህንነቱ የተጠበቀ እና ኣወንታዊ የትምህርት ኣከባቢ መፈጠር ላይ መሳተፍ።
- የሌሎችን መብቶች ማክበር እና ማሰብ።
- “የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ መሰረታዊ ሕጎች እና መመሪያዎች” እና የያንዳንዱ ትምህርት ቤት መመሪያ ማወቅ እና ማክበር።
- ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡ የደህንነት እና የጤና ችግር በማያስከትል መንገድ ባግባብ መልበስ።
- ለትምህርት ቤት ባልደረቦች ሲጠየቁ ማንነታቸው መግለጽ እና መመሪያቸውን መከተል እና ማክበር። እና
- የሌሎችን እና የትምህርት ቤት ንብረት ማክበር።



## የትምህርት ቤት ሓላፊነቶች

የትምህርት ቤት ባልደረቦች የሚከተሉት ሓላፊነቶች ኣሏቸው፤

- ደህነቱ የተጠበቀ እና መልካም የትምህርት ቤት ኣከባቢ እንዲፈጠር ማድረግ፤
- ተማሪዎችን ማወቅ፣ መንከባከብ እና መልካም ግኑኝነት መመስረት፣
- እያንዳንዱ ተማሪ ላይ በከፍተኛ ተስፋ ማኖር እና ጥራት ያለው ኣና ውጤታማ ትምህርት ማቅረብ፣
- ትህትና እና ኣክብሮት የተሞላበት ኣያያዝ ማሳየት፣
- የትማሪዎች ድምጽ እንዲሰማ የተለያዩ እድሎች ማቅረብ፣
- ትምህርት ቤት ያሉ ችግሮች ኣፈታት ላይ ቤተሰቦች እንዲሳተፉ ማበረታታት፣
- የሚፈጠሩ ችግሮችን ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲፈቱ ማበረታታት፣
- በት/ቤቱ ምክንያት የሚባክኑ የትምህርት ጊዜያትን መቀነስ ወይም ማስቀረት:
- የዲስፕሊን ዓላማ የባህሪ ለውጥ ላይ እርዳታ ለማድረግ እንጂ ለመቅጣት እንዳልሆነ መረዳት:
- ተጠያቂነትን ሊያስተምርና ግኑኝነትን ወደነበረው የሚመልስ እና ሊያድስ የሚችል ቅጣት መስጠት:

## አንድ ተማሪ ደንብ ከተላለፈ ምን ይሆናል?

አንድ ተማሪ ደንብን በመጣስ በሚከሰስበት ጊዜ የስነስርዓት ኣርምጃ ከመወሰዱ በፊት በበኩልህ ያለውን እውነት ለመምህርህ፣ ክውንስለር (ኣማካሪ)፣ ረዳት ርእሰ መምህር ወይም ርእሰ መምህር የመግለጽ መብት ኣላቸው። ወላጅ ከትምህርት ቤት ሰራተኞች ጋር ችግሩን ለማወቅ፣ መፍትሔ ለማፈላለግ ወይም ተገቢ ቅጣት ለመወሰን መገናኘት ይችላሉ። ሆኖም ግን ጥፋቱ ኣስከፊ ከሆነ ተማሪው ከትምህርት ቤት ልትታገድ ወይ ጠቕላላ ልትባረር ትችላለህ።

የትምህርት ቤት ኣስተዳዳሪ የኣንተ ክፍል ውስጥ፣ትምህርት ቤት ወይ የትምህርት ቤት ግዜ ውስጥ ወይ የሆነ የትምህርት ቤት ኣንቅስቃሴ ተማሪው መቆየት ለድህንነትህ ያሰጋል ወይም የትምህርት ሁኔታ ይረብሻል ብሎ ባሳማኝ ሁኔታ ካመነ በአስቸኳይ ተማሪውን እንዲያባርረው ሊያደርግ ይችላል: ተማሪው ከትምህርት ቤት ከታገደ፣ ጠቕላላ ከተባረረ ወይም ከኣደጋ ግዜ ከተባረረረ በ24 ውስጥ የተወሰደውን የስነስርኣት እርምጃ የሚገልጽ (ኖቲስ ኦፍ ዲሲፕሊነሪ ኣክሽን (NDA) ደብዳቤ ይደርስሃል።

## የተማሪ ባህሪ

## (ቀደም ሲል የተከለከለ ባህሪ ኮድ)

- ማቃጠል
- ማጥቃት
- አካላዊ ጥቃቶች
- ማጥቃት: ማስፈራራት እና ማዋከብ
- ቤት ሰብሮ መግባት
- ኮምፒዉተር ውስጥ ያለፈቃድ መግባት እና ማጭበርበር
- አደገኛ መሳሪያዎች
- አለመታዘዝ
- የመረበሽ ባህሪ
- የአልኮል መጠጦችን ማሰራጨት
- ሕጋዊ ያልሆኑ ኣደገኛ ዕጾች እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ነገሮች እና በሃኪም የሚታዘዙ ወይም ከሱፐር ማርከት ሊገዙ የሚችሉ መድሓኒቶች ማዘዋወር
- ማሪዋና ማሰራጨት
- ማስጨነቅ : ክፉ መሆን
- የውሸት ማስጠንቃቂያ
- የውሸት ሪፖርት
- በውሸት ማስፈራራት
- መደባደብ
- ርችቶች: ፍንዳታ: ኬሚካል
- የዱርዬ / የጥላቻ ቡድን እንቅስቃሴ
- የግድግዳ ላይ መጻፍ
- ማጥቃት
- ተገቢ ያልሆነ ወሲባዊ ምግባር
- ተገቢ ያልሆነ ቋንቋ
- አግባብነት የሌለው መነካካት
- በትምህርት ቤት ባለስልጣናት ላይ ጣልቃ መግባት
- የትምህርት ቤት ባለ ሥልጣናት ማስፈራራት
- የዝሙት አሠራር
- ተንኮል አዘቅት
- የተበላሸ ንብረት ጉዳት
- ኮምፒተርን አላግባብ መጠቀም
- ሌሎች ልዩ ባህሪያት
- አካላዊ ጥቃት
- መኮረጅ
- ሕገወጥ መድሃኒቶችን የተከለከሉ ንጥረ ነገሮች ይዞ መገኘት ወይም መጠቀም
- ህገወጥ መድሃኒቶች, የተከለከሉ ነገሮች, በሐኪም የታዘዘ መድሃኒት ወይም ያለክፍያ መድሃኒቶችን መያዝ
- የአልኮል መጠጦችን መያዝ ወይም መጠቀም
- ማሪንያዋን መያዝ ወይም መጠቀም
- የተሰረቀ ንብረት ይዞ መገኘት
- ዝርፊያ
- ደንብ-መስበር
- የአልኮል መጠጦችን መሸጥSelling
- ማሪዋና መሸጥ
- ወሲባዊ ጥቃት
- ትንሽ የታጠቁ ቢላዎች
- ስርቆት
- ለመግደል ማስፈራራት
- የመጫወቻ ሽጉጦችና የጦር መሣሪያ አሻንጉሊቶች
- እንደ መሳሪያዎች ጥቅም ላይ የዋሉ መጫወቻዎች
- መተላለፍ
- የትንባሆ ምርቶችን መጠቀም ወይም ይዞ መገኘት(electronic vapor devices)
- ቁማር መጫወት

የዲስፕሊን እርምጃ ማስታወቂያ (NDA) በ24 ሰዓት ውስጥ ይሰጣል::

## በ1989 የፌደራል ከኣደንዛዥ ዕጾች ነጻ የሆኑ ትምህርት ቤቶች እና ማሕበረሰቦች ድንጋጌ ለተማሪዎች እና ለወላጆች የሚጠይቀው ማሳሰቢያ

የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ተማሪዎች ኣልክሆል እና ኣደንዛዥ ዕጽ ትምህርት ቤት ግዚ ውስጥ ፤በት / ቤት ንብረት ውስጥ, በት / ቤት ስፖንሰር በተደረገ ትራንስፖርት ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ላይ መያዝ፣ መጠቀም ወይም ማከፋፈል ይከልክላል። ይህን ሕግ ማክበር የግድ ነው። ይህን ሕግ የሚጥሱ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ለረጅም ግዜ ሊታገዱ ወይም ጠቅላላ ሊባረሩ ይችላሉ። ሕገ ወጥ የሆኑ ዕጾችን ይዞ መገኘት ወይም መጠቀም እና ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ኣልኮሆል ይዞ መገኘት ወይም መጠቀም ስህተት ነው ብሎም ጤንነትን እና ትምህርትን ይጎዳል። የሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ የዕጽ እና ኣልኮሆል ምክር ኣገልግሎት ሊያዘጋጅ እና ሊያቀርብ ወይም የዕጽ እና ኣልክሆል ምክር ኣገልግሎት፣ ተሃድሶ ወይም ወደ ትምህርት ቤት መመለሻ ፕሮግራም በማዘጋጀት በኩል ሊረዳ ይችላል። ለተጨማሪ መረጃ የትምህርት ቤታችሁን ርእሰ መምህር ወይም ካውንስለር ኣነጋግሩ።



## አንድ ተማሪ በደል እንደተፈጸመበት አድርጎ ብይስብስ?

ርእሰ መምህሩ ወይም ምክትል ርእሰ መምህሩ የስነስርዓት ኣርምጃ ሊወስድብህ ከወሰነ እና የተመደበው ያስነስርዓት እርምጃ ተማሪው ተገቢ ኣና ፍትሃዊ ያለሆነ ነው ብለህ ካመንክ ተማሪው ውሳኔውን መቃወም እና ይግባኝ የማለት መብት ኣለህ። የተለያዩ የይግባኝ ኣፈጻጸሞች የተማሪዎች መብት ኣና ሓላፊነቶች የሚለው ጽሑፍ ላይ ይገኛል። ይህን ጽሑፍ ከትምህርት ቤትህ፣ ከዲሲፕሊን ኦፊስ በስልክ ቁጥር 206-252-0820 ወይም ከሲያትል ፓብሊክ ስኩልስ ዌብ ሳይት በሚቀጠልው ኣድራሻ፤ www.seattleschools.org ማግኘት ይቻላል።